ክብረ ክህነት እና የካህናት ተጋድሎ አበርክቶት በኢትዮጵያ

በመ/ር ኀይለማርያም
ዘውዱ

ቀን 02/08/2013 ዓ.ም

- ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማና። በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን? አለው።
- እርሱም። የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው። ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነው። ሐዋ፰፥፴፩

ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ ማቴ 8*4

ሁሉን የሚከፍቱ ቁልፎች

(master keys)



የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ.. ማቴ. 16*18

ኦርቶዶክሳዊ ይዘት

- አንዳቸው ያለአንዳቸው መኖር አይችሉም
- መገለጫቸው ቀስ በቀስ ነው።



ምሥረታ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሕሊና ሥላሴ የተወለዱ የቅዱሳን መላእክት እና ሁለተኛ ልደታቸውን ብጥምቀት ያገኙ ክርስቲያኖች ረቂቅ ሕብረት ናትና ለምሥረታ ።

ያልተቋረጠ አምልኮተ እግዚአብሔር

- ሕገ ልቡና
- ሕገ ኦሪት
- ሕገ ወንጌል

እሚነ
እግዚአብሔር

❖ አንዳቸው ያለአንዳቸው መኖር አይችሉም
❖ መገለጫቸው ቀስ በቀስ ፧በበንስቲት dynamics) ነው።



የቤተ ክርስቲያን መሠረቱ ክህነት ነው።





አርእስት

- የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ
- መግቢያ
- ሥልጣነ ክህነት በሕገ ልቡና
- የብሉይ ኪዳን ሥርዓተ ክህነት
- የሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት
- የክህነት አገልግሎት ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ አገልግሎት
- የሥልጣነ ክህነት የሥልጣን ወሰን
- **ሥርዓተ ክህነት ትሩፋት ለኢትዮጵያ**
- በሐዲስ ኪዳን የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች እና ሥርዓተ ሲመት
- የቅዱሳን አበው ካሕናት ተጋድሎ

የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ

- የሥልጣነ ክህነትን ምንነት ፣ ጠቀሜታ እና የሥልጣን ወሰን ማሳወቅ ፤
- ሥልጣነ ክህነት ለኢትዮጵያ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ማሳወቅ ።
- ሥልጣነ ክህነት ያላቸው አበው ቅዱሳን አባቶቻችን ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዓለም ሀገራት የተለየ የቅድስና ሕይወት፤ የነጻነት ሕይወት ፤ ሕዝቦቿ በከፍተኛ ሞራል ከፍታ እንዲኖር የገፈሉትን ዋጋ እና ተጋድሎ በመጠኑ መግለጥ ።

በር በበር

- ሃይማኖት (አምልኮተ እግዚአብሔር) ሦስት ነገሮች ላይ የቆመ ነው።
  - አንዳቸው ያለአንዳቸው መኖር አይችሉም
  - መገለጣቸው ቀስ በቀስ ፤በበንስቲት dynamics) ነው።

አሚነ ሥላሴ

ለምሳሌ (የቤተ ክርስቲያን መገለጥ)

1. ጊዜ ፍጥረት(የመላእክት እና የአዳም መፈጠር)
2. ሕይወተ አዳም በገነት ወደቂቁ በሕገ ልቡና ወበሕገ ኦሪት፤
3. ተሠግወተ ቃል እምድንግል(ቅድስት ቤተክርስቲያን በጉልህ የተገለጠችበት)
4. ምጽአተ ክርስቶስ በዐብይ ግርማ (ቅድስት ቤተክርስቲያን በምልአት እና በስፋት የምትገለጥበት)

ሥልጣነ ክህነት በሕገ ልቡና

በደብር ቅዱስ የነበረው የክህነት አገልግሎት፤

- የእንሥሣት መስዋእት መሰዋት
- ማሕበሩን (ቤተሰቡን) መጠበቅ፣ መምራት
- እግዚአብሔርን በቅድስና ማገልገል
- ስልጣኑ የሥጋ መቅሰፍቶችን ማራቅ ነው ።

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና እግዚአብሔርን የምታውቅ እና እግዚአብሔርን የምታመልክ መሆንዋን በጉልህ ከሚያመለክቱት መካከል ሁለቱ የሕገ ልቡና ካህናት ናቸው።

፩) ክሕነቱ የዘላለም የተባለለት መልከጼዴቅ (ዘእምነገዱ ለካም መጽ. ቀሌምንጦስ)

- የ፲ሩንም አርስተ አበው አጽም እንደታቦት አድርጎ በጎልጎታ(የራስ ቅል) ሲጸልይ፣ መስዋእት ሲሰዋ ኑሯል።
- በሕገ ልቡና የኖረ የሐዲስ ኪዳን ካህን ነው።
- አዲስ ኪዳንን በሕገ ልቡና የተመለከተ ካሕን ነው ።

- ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል(ዕብ ፯)

“የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤

ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው። የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፥ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው።

አባትና እናት የትውልድም ቍጥር የሌትም፥ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።

የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አስራት የሰጠው ይህ ሰው እንዴት ትልቅ እንደ ነበረ እስኪ ተመልከቱ።

ትውልዱ ከእነርሱ የማይቈጠረው ግን ከአብርሃም አሥራትን አውጥቶአል፥ የተስፋ ቃል የነበረውንም ባርኮአል።

ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው።

በዚህስ የሚሞቱ ሰዎች አሥራትን ያስወጣሉ፥ በዚያ ግን የሚያስወጣ በሕይወት እንዲኖር የተመሰከረለት እርሱ ነው።

ይህንም ለማለት ሲፈቀድ፥ አሥራትን የሚያስወጣ ሌዊ እንኳ በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቶአል፤

መልከ ጼዴቅ በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና። "

፪) ካህኑ ዮቶር አህማተ ሙሴ (ዘጸ ፲፰)

- በሚድያም በእግዚአብሔር ተራራ አካባቢ ይኖር የነበረ።
- እግዚአብሔርን የሚፈራ እና በአስተዳደር ጥበብ እና ብልሃት እጅግ የተካነ ።
- ለ፵ ዓመት በመንግስተ ፈርኦን ፣ ለተጨማሪ ፵ ዓመተ በበግ እረኝነት ያሳለፈውን ነቢዩ ሙሴን የባርነት ቀንበር ያኀበጠውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዴት መርቶ ወደ ቃል ኪዳኗ ምድር እንደሚያደርሰው ትልቅ የአስተዳደር ጥበብን ያመላከት ታላቅ ካህን

የብሉይ ኪዳን ሥርዓተ ክህነት

- ከዓለም ሕዝቦች መካከል ለአንድ የእሥራኤል ሕዝብ (በኋላ ኢትዮጵያ ብትጨመርም)፤
- ከአንድ ሕዝብ ነገዶች መካከል ደግሞ ለአንድ ነገድ ብቻ ።
- ከአንድ ነገድ ልጆች መካከል ደግሞ ለመጀመሪያ ልጅ የሚሰጥ ሥልጣን ነበር::
- የስልጣን ወሰኑም ምድራዊ ነው። በሥጋ ላይ የሚመጣን መከራ ፣መቅሰፍት ፣ ስደት እና ረሃብ ለመስቆም እግዚአብሔርን በመስዋእት፣ በጸሎት ጠይቆ

የቀጠለ....

- የካህናት አመራረጥ እና የሹመት ደረጃ
    - ሊቀ ካህናት
    - ካህናት/ሌዋውያን
    - መዘምራን
- የአለባበስ ሥርዓት
- የአገልግሎት ዓይነት
    - የእለት
    - የሳምንት
    - የዓመት

የሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት አገልግሎት

የሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት ምሥረታ

- “እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው።

ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ። አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።
ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።
እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።” ማቴ ፲፮፥፲፭-፲፱

- እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ። ዮሐ ፳፡፳፪

- ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው ዮሐ ፳፡፳፫

- እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

ክብረ ክህነት እንደ አባጊዮርጊስ አገላለጽ

ከፍጀቱ ፍጥረታት መካከል ለሰው ልጅ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ልዩ ጸጋ ነው።

በክህነት ሰማይ እና ምድር ፣ ሩቁ እና ቅርቡ ፣ ረቂቁ እና ግዙፉ ይገናኙበታል፤ ይገዙበታል ።

"ይህን እሳት ያለ ጉጠት

ሳይፈራ የሚዳስስ ካህን እንደምን ያለ ነው? ....

በመሰዊያው ላይ ይህን ህብስቱንየሚፈትተው ካህን እንደምን ያለ ነው?

....

ብላቴናውን በአባቱ ፊት በእናቱ ራስ ላይ አኑሮ የሚሰዋ ይመስላል!

የምስጢሩን ወይን በፅዋው የሚዘጋጀው ካህን እንደምን ያለ ነው?

ለዚህ ለማዘጋጀቱ አንክሮ ይገባል! የልጁን ደም በአባቱ ፊት በእናቱ ላይ

ሲንጠፈጠፍ

የሚቀዳን ይመስላል!

ክብረ ክህነት እንደ አባጊዮርጊስ አገላለጽ

“ሙሽራውን ያለ ወቅለምት የሚሰዋ ሙሽራይቱን የሙሽራውን ሥጋ እንድትበላ የሚጠራት ልጆቿንም በአባታቸው ሥጋ የሚያሳድጋቸው ይህ ካህን እንደምን
ያለ ነው? …
የእግዚአብሔርን በግ ለመሠዋት ጣቶቹ ወቅለሞት የሆኑለት ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው?
አንደበቱ መናፍቃንን ከመዕመናን ለመለየት ሰይፍ የሆነለት፣
ምዕመናንን ከአምላካቸው ደም ጋር አንድ የሚያደርጋቸው ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው?
ለዚህ አንክሮ ይገባል!” አርጋኖን ዘሰኑይ

ክብረ ክህነት እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አገላለጽ

- ‘’በምድር የሚከወን ግን በሰማያዊ ማዕረግ
- ራሱ ጌታችን ተሰውቶ፣ በመሰውያው ላይ ሆኖ ካህኑ ለመስዋእት በቀረበው ላይ ሲጸልይ.፣ ምእመናን በሙሉ በከበረው ደሙ ፈሳሽነት ነጽተው ስትመለከት በምድር ላይ እንደቆምክ ሁነህ ታስባለህን?
- ወዮ ምን ይረቅ? ወዮ እንደምን ይደንቅ? ለሰው ልጆች የተደረገው የእግዚአብሔር ቸርነት እንደምን ያለ ቸርነት ነው?
- ከባሕርይ አባቱ ከአብ ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከምንፈስ ቅዱስ ጋር በልዕልና የሚቀመጥ በዚያን ሰዓት ደግሞ በሁሉም ካህናት እጅ ተይዞ ይሠዋል ፤ ሊቀበሉት ሊዋሐዱት ለሚፈልጉት ሁሉ ራሱን ይሰጣል።

ከኦሪቱ ሥልጣን ጋር ሲነጻጸር (፩ኛ ነገ ፲፰ ÷፳-፳፱ ከነቢዩ ኤልያስ መሥዋዕት)

- ካህኑ በቤተ መቅደስ ሲቆም እንደኦሪቱ እሳት ከሰማይ እንድወርድ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ፤
- የተሰዋው መስዋዕት ከሰማይ የወረደው እሳት እንዲበላው ሳይሆን ፀጋ መንፈስ ቀዱስ በመስዋዕቱ ላይ ወርዶ ሁሉንም ነፍሳት እንዲቀድስ ፤ከወርቅም ይልቅንጹሐን እና ጽሩያን ያደርጋቸው ዘንድ ረዘም ያለ ምልጃን እና ጸሎትን ያቀርባል ።
- አብ ፍርድን ለወልድ ሰጥቶታል (ዮሐ ፭÷፳፪) ወልድም ፍርድን ለካህናትሰጥቷል ።
- ኃጢአታቸውውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል ፤ የያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል (ዮሐ ፳÷፳፫) ።
- ካህናት በመንፈሳዊ ልደት አምጠው ም እመናንን እንዳ ወለዱ እና በጥምቀት

የቀጠለ....

ቅ.ዮ.አ (የወላጆችን እና ካህናትን ኃላፊነት እና ሥልጣን ያወዳድራል)

- ከሥጋ ወላጆች ካህናት ይበልጣሉ
- የሥጋ ወላጆች ለዚህ ዓለም ብቻ ሲወልዱን ካህናት ግን ለዘለዓለም እና ለማያልፈው መንግስት ይወልዱናል።
- የሥጋ ወላጆች ከልጆቻቸው ሞትን ማራቅ ከበሽታ መጠቃት ነጻ ሊያደርጓቸው አይችሉም ካህናት ግን --
  ያዕ ፭÷፲፬-፲፭
- የሥጋ ወላጆች ልጆቻቸውን ከዚህ ዓለም ገዥዎች ቅጣት ሊታደጉቸው አይችሉም ካህናት ግን ከነገስታ


ተልእኮ ካሕናት
ያላመኑትን አስተምህሮ ወደ ኦርቶዶክሳዊት ዓለም መመለስ።
ያአመኑትን ማንጻት፣ ማጽናት እና መቀደስ።
• ማቴ፳፰፲፰÷፳
ሕግጋት ፤ ምህረት ፤ ቸርነት
ሃይማኖት
(ስውንና መላእክትን አንድ መንጋ ያደረገች ረቂቅ አምድ)
አምልኮ
የሉላዊነት፣ የሴኩላሪዝም፣ የፖስት ህዩማኒዝም እና የፖስት ሞደርኒዝም ዋና ዓላማ ምእመናንን ከኦርቶዶክሳዊት ዓለም እያዘናጉ ወደ ዓለመ አሕዛብ መውሰድ ።
ዓለመ መሬት
ዓለመ አሕዛብ
ኦርቶዶክሳዊት ዓለም

አገልግሎት ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ አገልግሎት

ትምህርተ ሃይማኖትን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እያስተማረ ያሳድገዋል።
የፈለገውን የህይወት መስመር እንዲከተል ያበቃዋል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያኛ

ከህኑ ከዓለም ለይቶ ከማህጸነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ዳግም ይወልደዋል

መለኮታዊዉን ስጋ እና ደሙ ይመግበዋል።



ሥጋ ደውየውን በጸሎተ ቀንዲል
በሽታውን በምስጢረ ንስ... ውሰዋል ።

ቅባ ሜሮን ቀብቶ መንፈስ ቅዱስን ያሳድሮበታል

ዓለም

መንግስተ እግዚአብሔር

....ግልገሎቼን አሰማራ
...ጠቦቶቼን ጠብቅ...
በጎቼን አሰማራ
ዮሃ ፳፩ ፥ ፲፭-፲፯

፲፯/፯/፳፲ ‘ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ዮሃ ፳፡፳፪ ’

<u>ያለሥልጣነ ክህነት ተግባራዊ የማይሆኑ ቃላተ ወንጌል</u>

እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው።
ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ
የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል።………….
 እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ
አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።
በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል፤
እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል።ዮሐ
፩ 1-6

፫

ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው።
እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ
ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ
ሕይወት የላችሁም።
 ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም
ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ።
 ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ
ነውና።
ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል
እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ዮሐ 6÷53

፪

ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት
እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።
 ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ
መንፈስ ነው። ዮሐ 3÷5-6

፬

 ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ
እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤
የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። ግሐ
፪÷፴፰

የሥልጣነ ክህነት የሥልጣን ወሰን



ከሥልጣነ ክህነት የሚቀዳው የቅድስት ቤተክርስቲያን ባሕርያት

ቅ. ቤ.ክ

ቅድስት

ሰላም ለክሙ ጻድቃን ወሰማዕት
እለአ እርፍክሙ በዛቲ እለት
መዋእያነ ዓለም አንትሙ በብዙህ
ት እግስት
ሰአሉ ቅድመ ፈጣሪ በኩሉ ሰዓት
እንበለ ንስሐ ኢይንስአነ ሞት

ቅዱሳን መላእክት

ኩላዊት/ዓለም አቀፋዊት/

ነፍሳተ ቅዱሳን /በገነት/

ክርስቶስ
(መስዋዕት + ክህነት)

በንስሐ ሕይወትየሚመላለሱ ምእመናን

አሐቲ

ሰላም ለክሙ ጻድቃነ ዛቲ እለት ክልክሙ
እድ ወአንስት በበአስማቲክሙ
ቅዱሳነ ሰማይ ወምድር ማሕበረ ሥላሴ አንትሙ
ዝክሩነ በጸሎትክሙ በእንተ ማርያም እሙ
ተማህጸነ ለክርስቶስ በስጋሁ ወበደሙ

ስውራን ቅዱሳን (በገጸ መሬት ያሉ)

ሐዋርያዊ
ት

ሥርዓተ ክህነት ትሩፋት ለኢትዮጵያ



በሐዲስ ኪዳን የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች እና

ሥርዓተ ሲመት

ዓበይት የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች

የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች

ሊቀ ጳጳሳት

ጳጳስ

ኤጲስቆጶስ

ቆሞስ

በድንግልና ሕይወት ሲወሰን (ሲመንኩስ)

በጋብቻ ሕይወት ሲወሰን

ቄስ

ዲያቆን

ንፍቀ ዲያቆን

አናጉንስጢስ

ዓጻዌ ሆኅት

መዘምራን

የድንግልና ሕይወት ቅድመ ሁኔታ ነው

መጀመሪያው ሕጻንነት ዲቁና መዳረሻው ልዕልና ክህነት ነው።

በንፍሐተ መንፈስ ቅዱስ እና በአንብሮተ እድ ብቻ የሚሾሙ ካህናት(ፍ.መ አንቀጽ)

ሊቀ ጳጳሳት

ጳጳስ

ኤጲስቆጶስ

ቆሞስ

ቄስ

ዲያቆን

ሊቀ ጳጳሱ በቃል ብቻ የሚሾማቸው (ፍ.መ አንቀጽ ፰)



በቡድን የመወያያ ጥያቄዎች

ቡድን አንድ ፡ የኢትዮጵያ ባሕል ከሥር ዓተ ክህነት ጋር ያለውን ግንኙነት አሳዩ?

ቡድን ሁለት ፡ ሀገር በቀል እውቀቶችን ዘርዝሩ እና በዝርዝሩ ላይ ስለ ካህናት አበርክቶት ተወያዩ?

ቡድን ሦስት፡ ሥርዓተ ክህነት በማሕበራዊ ሕይወት ላይ ያለውን በጎ ተጽእኖ ተወያዩ?

ቡድን አራት ፡

ቡድን አምስት ፡

ቡድን ስድስት ፡

የቅዱሳን አበው ካህናት ተጋድሎ

፩) ገዳማዊ ሕይወትን ከማስፋፋት አንጻር፡

ገዳማዊ ሕይወት በኢትዮጵያ በሕገ ልቡና በካህኑ በመልከጼዴቅ የተጀመረ ሲሆን በብሉይ ኪዳንም ተጠናክሮ እንደቀጠለ
ይታወቃል።

ገዳማዊ ሕይወት ለኢትዮጵያ በርካታ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት ። ለምሳሌ

- የሰብከተ ወንጌል ማዕከል በመሆን ኢትዮጵያን የቃለ እግዚአብሔር መፍሰሻ አድርገዋል።
- ክርስቲያናዊው ማህበረሰብ በእለት ከእለት ኑሮው የቅድስና ሕይወትን እና ምግባራትን እንዲለማመድ አድርጓል።
- ማሕበራዊ ስነምግባራት አብዛኛዎቹ ከገዳማት የሚቀዱ ናቸው።
- ኢትዮጵያን ሌሊት በሰዓታት ቀን በጸሎት ይጠብቃል።
  - እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይደክማል መዝ ፻፳፯ ÷፩
- ኦርቶዶክሳውያን የመንፈስ መረበሽ፣ የአእምሮ መታወክ ሲገጥማቸው የጽሙና ጊዜ በገዳሙ ውስጥ አሳልፈው ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ትልቅ አስተዋጾ አለው።
- አብዛኛዎቹ ገዳማት የተአምራት እና የፈውስ ቦታ ስለሆኑ ለምእመናኑ ፈውሰ ሥጋ እና ፈውሰ ነፍስ ይሰጣሉ ።

ገዳማዊ ሕይወት በኢትዮጵያ ካስፋፉ አበው ቅዱሳን መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው

ተስዓቱ ቅዱሳን ፡

ተስዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ480 ዓ.ም. በመንግሥት አልአሜዳ ዘመን ሲሆን የመጡበትም ዐቢይ ምክንያት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ያስተማረውንና የተሰዋለትን ቀጥተኛውን ትምህርት ተቀብለ በመከተላቸውና በ451ዓ.ም የተደረገውን የኬልቄዶን ጉባኤ ባለመቀበላቸው ከቢዛንታይን መንግሥት በደረሰባቸው የስ ስቃይ ምክንያት ነው።

እነዚህ ቅዱሳን ኢትዮጵያን እንደተወለዱባት አገር ቆጥረው ክርስትናን በሚገባ አስተምረው አስፋፍተዋል። እስከዛሬ ድረስ በስማቸው የሚጠሩትን ሌሎችንም ገዳማት መሥርተዋል።

የቤተ ክርስቲያኒቱን የግእዝ ቋንቋ በሚገባ አውቀው ቅዱሳት መጻሕፍትን ከክርስትና ከጽርእ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መልሰዋል፤ ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን በሚገባ ፈጽመው ስላረፉ ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች። ስማቸው፣ ገዳማቸውና የዕረፍት ቀናቸው እንደሚከተለው ነው።

ስም	ገዳም	የዕረፍት ቀን
አባ አሌፍ	ብጉዛን (አህስአ)	መጋቢት 11 ቀን
አባ አረጋዊ	ደብረ ዳሞ	ጥቅምት 14 ቀን
አባ አፍጼ	ዮሃ (የሐ)	ግንቦት 12 ቀን
አባ ሊቃኖስ	ደብረ ቆናጽል	ኅዳር 21 ቀን
አባ ገሪማ	መደራ	ሰኔ 17 ቀን
አባ ጉባ	ገርዓልታ	ግንቦት 29 ቀን
አባ ይምአታ	ገርርዓልታ	ጥቅምት 23 ቀን
አባ ጽንጠሌን	አክሱም አጠገብ	ጥቅምት 6 ቀን
አባ ጽሕማ	ጼዴንያ	ጥቅምት 16 ቀን ነው።

- ከሮም ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ የመጀመሪያ ሥራ ያደረጉት የኢትዮጵያን ቋንቋ እና ባሕል ማጥናት ነበር (በቅዱስ ያሬድ ቤተ ቀጢን ጉባዔ ቤት) ።
- የግእዝን ቋንቋ በሚገባ ተምረው በርካታ መጻህፍትን ከሱርስት እና ከጽርእ ወደ ግእዝ ተርጉመዋል።
- ገዳማዊ ሕይወትን አስፋፍተዋል፤ እስከ አሁን ድረስ በስማቸው የሚጠሩ ገዳማት አሉ ።
- ከቅዱስ ያሬድ ጋር በመሆን ኢትዮጵያን በመዘር

ቅዱስ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ፡

የቀጠለ…

ብሉያትን እና ሐዲሳትን በሚገባ የተማሩ ፤ በሠላሳ ዓመታቸው ደብረ ዳሞ በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን በመፈጸም ወደ ደሴ በመሄድ የሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳምን መስርተዋል። ገዳሙ በወቅቱ ትልቁ የኢትዮጵያ የልህቀት ማዕከል ነበር ።

ከዚህ ገዳም ስምንት መቶ ቅዱሳን አበው ሊቃውንት ፈልቀዋል። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- አቡነ በጸሎተ ሚካኤል
- አቡነ ተክለሃይማኖት ሐዋርያዊ
- አቡነ ሒሩተ አምላክ
- አቡነ አሮን
- አቡነ ገብረ ናዝራዊ
- አቡነ ሕዝቅያስ
- አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ
- አቡነ ዮሴፍን
- አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

የቀጠለ...

ቱ ከዋክብት፡

ዚህ ገዳማውያን ቅዱሳን በአጼ አምደ ጽዮን ዘመን በ፲፫፻፷ ዓ.ም የነበሩ የጣና ሀይቅን በገዳማዊ ቅድስና
ዲያሸበርቅ ያደረጉ (የመሠረቱ) ፤ ስብከተ ወንጌል በእጅጉ እንዲስፋፋ ያደረጉ ናቸው ።

- ❖ አቡነ በትረ ማርያም ዘዘጌ
- ❖ አቡነ ዘዮሐንስ ዘክብራን
- ❖ አቡነ ታዴዎስ ዘደብረ ማርያም
- ❖ አቡነ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤ
- ❖ አቡነ አሳይ ዘማን እንዳባ
- ❖ አቡነ ዘካርያስ ዘገሊላ
- ❖ አቡነ ኖብ ዘጎርጎራ

የቀጠለ...

ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ አቡነ ተክለሃይማኖት፡

ትምህርት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እና የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች የልህቀት ማዕከል እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻ

የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ ፬ቱ ጉባኤ ቤቶች

የመጻሕፍት ጉባኤ ቤት

የዜማ ጉባኤ ቤት

የቅኔ ጉባኤ ቤት



የንባብ ጉባኤ ቤት

ቅዱስ ያሬድ



የቅዱስ ያሬድ የዜማ ዓይነቶች



የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች

መጽሐፍ ቅዱስ

የሥነ ፍጥረት ምሳሌ የሆኑት ሃያ ሁለት አርእስተ ዜማ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ቀዜማ
2. በሐምስት
3. እግዚአብሔር ነግሠ
4. ይትባረክ
5. ሠለስት
6. ሰላም
7. መዝሙር /አቡን
8. ዘአምላኪየ
9. ሚበዝኁ
10. አርባዕት
11. ብፁዕ ዘይሴቡ
12. መወድስ
13. ኵልክሙ
14. ዕዝል
15. ዘይእዜ
16. ማኅሌት
17. ስብሐተ ነግህ
18. እስመ ለዓለም
19. አርያም
20. ክብር ይእቲ
21. ዝማሬ
22. ዕጣን ሞገር

፷) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ



- በቅዱስ ያሬድ ወንበር ተቀምጦ አስተምሯል።
- በዘመኑ የነበሩት የኢትዮጵያው ንጉሥ አፄ ይሳቅ

ከነበረው የመጻሕፍት እውቀት፤ ከአንደበተ ርቱእነቱ እና ከሰላው የስነጽሁፍ ችሎታው አንጻር

‘ኢትዮጵያዊ ቄትርሎስ፤ ኢትዮጵያዊ አፈወርቅ’ ብለው እንደጠሩት በታሪክ ተመዝግቧል።

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሥራዎች ፡

1. መጽሐፈ አርጋኖንን፤
2. » ምስጢርን፤
3. » ሰዓታትን፤
4. » እንዚራ ስብሐትን፤
5. » ሕይወተ ማርያምን፤
6. ውዳሴ መስቀልን ፤
7. ተአምኖ ቅዱሳንን፤
8. ክብረ ቅዱሳንን፤
9. ጸሎት ዘበእተ ቤትን
10. ጸሎተ ማዕድን፤
11. መኣዛ ቅዳሴን፤
12. ኖኅተ ብርሃንን፤
13. ፍካሬ ሐዋርያትን፤
14. ውዳሴ ሐዋርያትን፤
15. ውዳሴ ስብሐትን፤
16. የነቢያት፤ የሐዋርያት፤ የጻድቃንና የሰማዕታት፤ የመላእክትና የሊቃነ መላእክትን ውዳሴ (ሰላምታ) የተባሉትን መጻሕፍት ደርሰው ያበረከቱ ኢትዮጵያዊ ሊቅና ጻድቅ ናቸው።

በመጻሕፍት ጉባኤ ቤት የዐራት ዓይና መምህራን የዘር ሐረግ

የታች ቤት መምሕራን የዘር ሐረግ	የላይ ቤት መምህራን የዘር ሐረግ
መምህር አብራንዮስ	ጌታው ዮናስ
መምህር ሥነ ክርስቶስ	ጌታው ሰርፀ ድንግል
መምህር ኤስድሮስ (፫፰ መጻሕፍትን ያነበቡ)	ጌታው ወልደ ማርያም
አለቃ ወልደ አብ (፷፰ መጻሕፍትን ያነበቡ)	ጌታው መዝሙረ ድንግል

- የቅኔ ፈላስፋው ዮሃንስ ገብላዊ የሚከተሉትን ወላድያን ቅኔ አፍርቷል።



ሥዕል ፩፡ ሐረገ ዘርእ ዘልደተ ቅኔ

የቀጠለ...

ቦኑ ተአምር ከመ ይትቀነዩ ፣ ለበረድ በረድ ወመብረቅ ለመብረቅ ፤

ለምንት ውእቱ ተቀንዮትከ በወርቅ ፤

እሩቅ ብእሲ ለብእሲ ዕሩቅ፤

ዓለመ ሕይወቱ ዘየኀልቅ፤

ወሰማየ አጽሙ ይትከደን ደመና መቃብር ዕሙቅ፤

በኢዮር እንዘ ሀሎ አምላከ ኢዮር ምጡቅ፤

ዘይፌትሕ በኀጥእ ወይፌትሕ ለጻድቅ፤

አምጣነ ጽጌ ዓለም ሠርፀ መደልዋን አዕጹቅ

ጽብሐ ይሠርጽ ወሠርከ ይወድቅ ።

/ዘተዋናይ/

የአበው ሊቃነ ጳጳሳት ተጋድሎ፡

በርካታሊቃነ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያ መልክ እና መገለጫ እንድትሆን አድርገዋል። ዋና ዋናዎችን ለመጠቆም ያክል።

፩) አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን

- በኢትዮጵያ የአዲስ ኪዳን ክህነት ጀማሪ
- ወንጌልን በኢትዮጵያ ያስፋፉ ያስተማሩ
- የሠሯቸው ሥራዎች
  - ✓ በየቀበሌው የመካሪ ካህን ሥርዓት
  - ✓ የአበልጅ ሥርዓት/የክርስትና አባት እና ልጅ/
  - ✓ የቅዱሳን መጻሕፍት ወደግእዝ ቋንቋ

፩) ሰማእቱ አቡነ ጴጥሮስ

ብፁእነታቸው ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ በጠላት የጥይት እሩምታ እስከተገደሉበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሂደት 'ኮርየር ዴላሴራ' (corriere della sera) የተባለው ጋዜጣ ወኪል እና
የምስራቅ አፍሪካ ዜና መዋዕል አዘጋጅ የነበረው 'ፖጃሊ' የተባለ ጋዜጠኛ እ.ኤ.አ. ሰኔ 15 ቀን 1936 ዓም

"[illegible] ፅ
[illegible]ቸውና ትሕትናቸው ከገጻቸው የሚነበብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለብሰውት የነበረው ልብሰ ጵጵስና ጥቁር ካባ ያውም በጭቃ የተበከለ ነበር። በዚህ ሁኔታ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ችሎት ቀረቡ። ለፍርድም የተሠየሙት ዳኞች ሦስት ሲሆኑ እነዚህም ጣሊያኖችና የጦር ሹማምንት ናቸው።

የመካከለኛው ዳኛ ኮሎኔል ነበር። የቀረበባቸውም ወንጀል 'ሕዝብ ቀስቅሰዋል፣ ራስዎም አምፀዋል፣ ሌሎችንም እንዲያምፁ አድርገዋል' የሚል ነበር። ዳኛውም 'ካህናቱም ሆኑ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቂርሎስም የኢጣሊያንን መንግሥት ገዢነት አምነው አሜን ብለው ሲቀበሉ አርስዎ ለምን አመፁ፣ ለምን ብቻዎን አፈንጋጭ ሆኑ?' ሲል

፪) ሰማእቱ አቡነ ጴጥሮስ

'አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ ናቸው፣ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገዳቸው ነገር የለም። እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ። ሐላፊነትም ያለብኝ የቤተ ክርስቲያን አባት ነኝ። ስለዚህ ስለ ሀገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ አቆረቆራለሁ። ከዚህ በቀር ለእናንተ ችሎት የማቀርበው ነገር የለኝም። ለፈጣሪዬ ብቻ የምናገረውን አናገራለሁ። እኔን ለመግደል እንደወሰናችሁ ዐውቃለሁ። ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ። ግን ተከታዮቼን አትንኩ' አሉ።

ይህንንም ብለው በጥይት ተደብድበው ሲገደሉ እንዲያይ ተጋብዞ ለተሰበሰበው ሕዝብ የሚከተለውን ሕያው መልእክት አስተላለፉ።

''አረማዊ የሆነው የፋሺስት መንግሥት ቤተክርስቲያንን ለማቃጠል፣ ሕዝበ ክርስቲያንን ለመግደል፣ ሃይማኖትን ለማጥፋት፣ ታሪካችንን ለማበላሸት የመጣ ነው፡ እንጂ በጎ ለመሥራት፣ እውነተኛ ፍርድ ለመስጠት ስላልመጣ ለዚህ ለግፈኛ አትገዙ። ስለ ውድ ህገራችሁ፣ ስለ ቀናች ሃይማኖታችሁ ተከላከለ። ነጻነታችሁን ከሚረክስ ሙታቹህ ስማችሁ ሲቀደስ ታላቅ ዋጋ ያለው ክብር ታገኛላችሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚህ ለጠላት እንዳይገዛ አውግዣለሁ፤ የኢትዮጵያ መሬት ጠላትን ብትቀበል የተረገመች ትሁን። በፈጣሪየ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተገዛላችሁ ትሁን።''

- ለሀገር እስከየት ድረስ ዋጋ ሊከፈል እንደሚችል አሳይተዋል፤
- በሞታቸው የግፈኞችን ምኞት ከንቱ አድርገዋል፤ የኢትዮጵያን የመከራ ጊዜ አሳጥረዋል።
- የትውልድ የነጻነት ምልክት ሁነው አልፈዋል።

፫) ሰማእቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

- ❖ አብዛኛው ሊባል በሚችል ደረጃ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትመራባቸው የቤተ ክህነት መዋቅር ሠርተዋል፤
  - ✓ የሰበካ ጉባኤ ሥርዓት
  - ✓ የሰንበት ትምህርት ቤት
  - ✓ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበት ደንብ(ቃለ ዓዋዲ)
  - ✓ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት
  - ✓ የቅድስት ሥላሴ ሥነ መለኮት ኮሌጅ
  - ✓ ቤተክርስቲያን በገቢ ምክንያት እንዳትቸገር የገቢ ማስገኛ በርካታ ሕንፃዎችን አስገንብተዋል
- ❖ "አባ ቴዎፍሎስ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባቷ ብቻ ሳይሆን እናቷም ጭምር ነበር ለቤተክርስቲያኗ እድገት ያልሆነው ፣ ያላደረገው የማያደርገው አልነበረም" አባ ሸኖዳሣልሳዊ

፳) አቡነ ማቴዎስ ግብፃዊ የኢትዮጵያ ጳጳስ

አድዋ ጦርነት በስኬት እንዲጠናቀቅ ያበረከቱት አስተዋጽ፡

ከጦርነቱ በፊት፡

- ❖ የገበሬው ወታደር ከፍተኛ የስነልቡና ዝግጅት እንዲያደርግ
- ❖ ሴቶቹ ስንቅ እንዲያዘጋጁ
- ❖ ንስሐ እንዲገቡ

‘’**በጉዞው ወቅት**
በሊቀጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና በእጨጌ ወ/ጊዮርጊስ
አስተባባሪት መንፈሳዊ አገልግሎቱ
በመዓልትና በሌሊት በሰዓታት፣ በማኅሌት፣ በቅዳሴ በነግህና
በሰርክ ጸሎት ሳይቋረጥ ይከናወን ነበር።
ዘማቾቹም በሰንበት ቀን አለመጓዝ፣ ዓበይት በዓላትን
ማከበር፣ለድኃው መመጽወት እና የመሳሰሉትን ሃይማኖታዊ
ግዴታቸውን ያከናውኑ ነበር።” ቀሲስ መንግስቱ

ከዓፄ ምኒልክና ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በኅብረት የዓድዋን ጦርነት
የተካፈሉት ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ
ከሞሪስ ደኮፔ

የመወያያ ጥያቄዎች፡

የምዕራባዊ መጤ ባሕሎች ወረራ
እና የምእመናን ተጋላጭነት

የገለፃው ዓላማ

1. ኢትዮጵያዊ ባሕልንና ማነትን እንዲሁም ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖትን በዓላማ የሚንዱ መጤ ባሕላትን እና ልምምዶችን ተረድቶ መከላከል እና ማስወገድ፡፡
2. ኅብረተሰቡ ከነዚህ ስነልቦናዊ፣አካላዊ እንዲሁም ማኅበራዊ ግንኙነትን ከሚጎዱ መጤ ባሕሎች ራሱን እንዲጠብቅ ማንቃት፡፡
3. ኦርቶዶክሳውያን የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ፖሊሲ አርቃቂዎች፣ ፖለቲከኞች ፣የሚዲያባለሙያዎች ፣ነጋዴዎች እነዚህ መጤ ባሕላትን

ይዘት፡-

ሀ. መጤ የበአላት ዕለታት በ/ት ተቋማት እና በኅብረተሰቡ ውስጥ

ለ. ሌሎች መጤ ልምምዶች እና በዓላት

ሐ. የመጤባሕሎች መቢያ መንገዶች

መ. ምን እናድርገ(ምንተ ንግበር)

መግቢያ

እኛ ማን ነን ?

፩. ከአብራከ ሥላሴ በጥምቀት የተከፈልን ፤ በቅብአ ሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የተቀበልን ፤ የዘለዓለም ሕይወት የሆነውን ሥጋውን ደሙን የታደልን ፤ ፯ቱ (ም.ክህነት፣ ም.ጥምቀት ፣ ም. ሜሮን ፣ ም. ቁርባን ፣ ም. ንስሐ ፣ ም. ተክሊል፣ ም. ቀንዲል) ምስጢራት አጥር ቅጥር በሆኑላት ፣ በክህነታዊ አገልግሎት በምትመራው መንግሥተ እግዚአብሔር (ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ የወይኑ ግንድ ቅርንጫፎች ሆነን የምንኖር የእግዚአብሔር ልጆች ነን ።

በክህነት አገልግሎት የሚመራው ረቂቅ ዓለም



የኦርቶዶክሳውያን መገለጫ ጸባያት በጥቂቱ

1) ከሁለት ልደት የተገኘ ውሕድ ማንነት (ከባሕርዩ አዳም የተገኘች ልጅነት እና ከባሕርዩ ሥላሴ የተገኘች ልጅነት ውሕድ ማንነት) ያላቸው ናቸው ።

2) ዘለዓለማዊ በሆነው ክሕነታዊ መንግሥት (መንግሥተ እግዚአብሔ) ውስጥ የሚኖሩ ናቸው ።(ክርስቲያኖች በፈቃደ ክህነት ብቻ ፣ በሚያልፈውም ዓለም ይሁን በማያልፈው ዓለም ይኖራሉ ።)

3) ከግዘፍ (ከሥጋዊ) ወደ ርቀት (መሠወር) የሚያድግ የቅድስና ጽጋ አላቸው ። (ዐሥሩን የቅድስና ደርጃዎች ማሰብ ነው ። ንጽሐ ሥጋ ፣ ንጽሐ ንፍስ እና ንጽሀ ልቡና)

4.) የማየት አቅጣጫቸው ከውስጥ ወደ ወጭ፤ ከርቀት ወደ ግዘፍ ነው (የክህነትን እይታ ይመለከታል)፡፡

- ክህነት የተገኘው ረቂቅ ከሆነው መለኮት ነው ፡፡ ክህነት ረቂቁን እና ግዙፉን ዓለም የሚያገናኝ ብቸኛ ድልድይ ነው ፡፡ ከክህነት ውጭ ዓለመ ሰማያትን እና ዓለመ መሬትን የሚያገናኝ ስልጣን የለም ፡፡
  - ክህነት ድልድይ ነው (ሰማይ እና ምድርን የሚያገናኝ) ፡፡ ማቴ 18፡ 18
  - ክህነት ጨው ነው (የዓለምን አልጫነት የሚያጣፍጥ) ፡፡ ማቴ 5፡ 13
  - ክህነት ብርሃን ነው (የዓለምን የኀጢአት ጨለማ የሚያስወግድ)፡፡ማቴ 5፡ 14

- ክህነት ለሚመራት ቅድስት ጉባኤ ከውጭ ወደ ውስጥ የሚገባ/ የሚመለከት ዓይን ወይም ሐሳብ ውድቀትን ያስከትላል ፡፡

ለምሳሌ፦ ድቀተ አዳምን እና ሔዋን ፤ ድቀተ ዲያብሎስን ያስታውሷል፡፡

5.) ዓለምን (ስነፍጥረትን) የሚመለከቱበት እና የሚረዱበት የእውቀት መለኪያ በእግዚአብሔር መገለጥ የተገኘው ትምህርተ ሃይማኖት ነው።

- በስሜት ሕዋሳት የተገኘውን እውቀት --------> በአእምሮአዊ እውቀት ያነጥሩታል።
- በአእምሮ ስሌት(ፍልስፍና እና ሣይንስ) የተገኘውን እውቀት --------> የእምነት ማረፊያ በሆነችው የልቡና እውቀት (እምነት)ያነጥሩታል ።
- በልቡና (እምነት) አማካኝነት የተገኘው እውቀት ፣ እውነት እና ሕይወት ነውና ይኖሩታል ።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑልንን መአዛ ክህነታቸው ለዓለም የተረፈውን የዓለም መሪውችን ቅዱሳን አባቶችን መመልከት ያሻል ።

- ኢትዮጵያውያን አባቶች
  - ቅዱስ ያሬድ
  - አባ ኢየሱስ ሞአ
  - አባ ጊዮርጊስ
  - አባ ተክለሃይማኖት

እስክንድርያውያን አባቶች

- ቅዱስ አትናቴዎስ
- ቅዱስ ቄርሎስ
- ቅዱስ ዲዮስቆሮስ

ቀጰዶቅያውያን አባቶች

- ቅዱስ ባስልዮስ
- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ
- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ
- ቅዱስ ኤፍሬም
- ቅዱስ ኤጲፋንዮስ

ኦርቶዶክሳውያን ከውጭ የሚመጣውን እውቀት ባሕል እንዴት ይቀበሉታል ?

- የሰውን ልጅ ድኅነት ማእከል ሲያደርግ ፤
- የሰውን ልጅ ስነ ፍጥረት የተረዳ ሲሆን፤
- የፍጥረት ሁሉ መገኛ፣ መጨረሻ እና ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ያገናዘበ ሲሆን ።

መጤ የበአል ዕለታት በትምህርት ተቋማት

‘

- ቫላንታይን ዳይ
- አፕሪል ዘፉል
- ክሬዚ ዳይ
- ከለር ዳይ
- ኦልድስ ዳይ
- ቤቢ አይ
- ዋተር ዳይ
- ቲቪ
- ኤች አይ ቪ
- ወባ

ዓላማው፡

የበአሉ አከባበር መገለጫዎች

- ዕለቱ የተወሰነ ቀን የለውም ነገር ግን በስምምነት በሚወሰን ቀን ይካሄዳል።
- ተመራቂ ተማሪዎች አልያም ከፍ ያለ ክፍል ደረጃ ባሉ ወጣቶች ተዘጋጅቶ ይከበራል።
- የተተለተለ ልብስ ፣ የነተበ ጫማ እንዲሁም ቅጥ የለሽ የጸጉር አሰራር በማድረግ ።
- በዘፈን ፣ በጭፈራ ፣ በስካር ታጅቦ በድሪያና በዝሙት የሚደመደም ዕለት ነው።
- የሃይማኖት ሕጎች፣ የትምህርት ቤት ሕጎች ፣ ማህበረሰባዊ ገደቦች ፣ ሀገራዊ ሕጎች የሚጣሱበት ሲሆን አፈንጋጭነት እና ሕገ ወጥነትን የሚለማመዱበት ቀን ነው።

የቀጠለ....

- ከዚ በፊት ታይቶ የማይታወቁ ተግባራት ስለሚተገበርበት ወጣቶችን ለአፈንጋጭነት ደፋር እንዲሆኑ ያደርጋል።
- ዕለታቱ ሲከበሩ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግቢ የሚገኙ ዕጻናት አሉታዊ ተጽእኖ ያድርባቸዋል።
- የበዓሉ አስተባባሪዎች እና ተግባሪዎች በአመዛኙ የብሔራዊ ፈተና ወሳጅ የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆናቸው በዓላቱን ከማዘጋጀት እስከ ማክበር ባሉ ሒደቶች በመጠመድ ከትምህርት ይታጎላሉ እነርሱም፦

(የበዓል እቅድ ማውጣት ፣ ስብሰባዎችን ማድረግ ፣ የገንዘብ መዋጮ መሰብሰብ፣ግብዓቶችን መግዛት ፣ በዓሉን ማስተባበር ፣ ግብዓቶችን መመለስ፣ድህረ ፓርቲ ማዘጋጀት. . . . .)

Sweet
Selfie

2 . የፍቅረኞች ቀን(**Valentine** Day)

የበዓሉ ታሪካዊ አመጣጥ

- በጣልያና ሀገር የሚኖሩ ቄስ ቫለንታይን የተባሉ የካቶሊክ መነኩሴ ጋብቻ በተከለከለበት ወቅት ጥንዶችን በማጋባታቸው በሞት ስለጠቀጡ ለመታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ ተከታየቻቸው ያስጀመሩት ልምድ ነው።
- የበዓሉ አክባሪዎች ወጣት ጥንዶች ሲሆኑ ቀይ ልብስ፣ቀይ ቆብ፣ቀይ የአንገት ልብስ፣ ቀይ የእጅ ቦርሳ፣ ቀይ መጫሚያ፣ቀይ ክራቫት . . .ወዘተ በማድረግ ሴቶቹ በእጃቸው ቀይ ጽጌሬዳ በመያዝ ወደ አደባባይ ለታይታ ይወጣሉ
- አልባሳቱና ቁሳቁሶቹ ቀያይ መሆናቸው የፈሰሰውን የሟቹን የካቶሊክ ቄስ ደም መፍሰስ ለማሰብ ነው።
- በሀገር ውስጥ ኤፍ ኤሞች መገናኛ ብዙአን በይፋ የዝሙትና የስካር ድግሶች በስፋት ይተዋወቃሉ።
- በዕለቱ በተለይ በክልል ከተሞች በርካታ ልጃገረዶች እና ደናግላን ወንዶች ቅድስናቸውን የሚያጡበት ዕለት ነው።

www.ethiopianreporter.com


Harmony Hotel
Special Valentine's
dinner party
@
Harmony Hotel
- First Class Buffet Dinner
With Wine
- Best New Artist Of The Year
Michael Lemu Demisew
With Express Band
- Stand-Up Comedy
- Surprise Artist
- Surprise Gifts
- Photo program by Photo zola
-More Entertainment
MICHAEL
Lemma Demisew
JORKA

አዲስ በጣም አስቂኝ ቀልድ
ቫላንታይን
Habtsh studio
ሀብቴ+ድርሹ

በማሲንቆ
ዘና ፈታ ይበሉበት
VALENTINE'S
DAY

3. የማሞኛ ቀን(APRIL The Foul)

- የሚያዝያ የመጀመሪያ ቀን ላይ የሚከበር ቀን ነው።
- ዓላማው በውሸት ሰዎች ማስደንገጥ ነው።
- አፈጻጸሙ ድንገቴ የሆኑ አስደንጋጭ እና አስገራሚ ክስተቶች እንደተደረጉ አድርጎ ማቅረብ እና መናገርን ያካትታል።
- ንግርቶቹ ሙሉ ለሙሉ ውሸት የሆኑና የሰሚውን ስሜት የሚነኩ ናቸው።
- በከተሞች በስፋት እየተለመደ የመጣ ሲሆን መጤ በዓላትን ሳይመረምር በሚቀበለው ወጣት ዘንድ እየተዘወተረ ይገኛል።

"ይርሀቁ ወይጉየዩ ሠራዊተ ዲያብሎስ አጋንንት .... ዘመዓልት ወዘሌሊት ዘቀትር ወዘሰዓት እምነግህ እስከ ሰርክ ወእምሰርክ እስከ ንግህ እለ ያደነግጹ ነፍሰ ወሥጋ "

ለ. ሌሎች መጤ ልምምዶች እና በዓላት

1. ገና ወይም ክሪስማስ

- የፈረንጆች ክሪስማስ የዘመን መለወጫ ዕለታቸው ሲሆን የክርስቶስን ልደትን እያከበርን ነው ይላሉ።
- የምዕራባውያን ክሪስማስ አጀማመር እና አከባበር የሳተርን(የጸሃይ) አምላክን ለማሰብ እና ለማምለክ ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ የሚከናወን ነበር።
- ከ4ኛው ክፍለ ዘን ወዲሂ ክራይስተ ማሰ(የጌታ በዓል) በሚል ሲቀይሩት ከቀደመው የጣኦት አምልኮ የወረሳቸውን እንደ የገና ዛፍ፣የገና አባት፣ቀያይ ቁሳቁሶች፣ . . . . ወዘተ አብሮ ተቀብሎ እያከበረ ይገኛል
- የ "ገና አባት "፣ "የገና" ዛፍ፣ በረዶ፣ሻማ፣ዛፉ ላይ የሚደረጉ ነገሮች አምልኮተ

ሳንታ ክላውስ(የገና አባት)

ሀ. ታሪካዊ አመጣጡ እና አምልኮታዊ ጠባዮቹ

- የገና አባት ሴንት ኒኮላስ የተባለ የሀይምነት አባታቸው የፈጠረው ሃሳብ ሲሆን እርሱን ለመዘከር ሲባል መሰል ተግባር ያከናወናል።
- በአሜሪካ ሕጻናት ዘንድ ክራምፐስ የተባለው ባለ ቀንድ የገና አባት መጥፎ ሕጻናትን ወደ ሲዖል ለመከተት ይመጣል ተብሎ ይታመናል።
- በጎ እና ክፉ አምላክ ከሚሏቸው አማልክት መካከል በበረዶው ውስጥ የሚደበቀውን ጣዖት ለማሰብ በዛፉ ላይ በረዶ(በእኛ ሀገር በረዶ ስለሌለ ጥጥ) ያደርጋሉ።

የገና ዛፍ

ሀ. ታሪካዊ አመጣጡ

- የጥንት ግብጻውያንና ከምድር ወገብ በስተ ሰሜን ማህበረሰቦች ፀሀይን እነደ አምላክ ከከቆጥሩ ነበር በመሆኑም በክረምት ወራት ይህ የፀሀይ አምላክ ችግር ገጥሞታለ ወይመ ደክማለ ብለው ያስባሉ።
- በመሆኑም ዲሴመበር 21/22 ላይ ይህ የፀሀይ አምላክ ደህና እአሆነ ነው ዌወም እየተሻለው ነው በማለት ቤታቸውን በአረንጋዴ ተክሎች ያስጌጣሉ
- በመሆኑም ለጣኦት አመልኮ አገልግሎት የሚውል ነው።

መ. ሌሎች መጤ ልምምዶች እና በዓላት

መጤ ልምምዶች

1. ዮጋ
2. የአደንዛዥ ዕጽ ሱሰኝነት

ንዴት:ውጥረት:ጭንቀት ለማምለጥ የሚዘወተሩ ስልቶች

- ከፍተኛ አልኮል መውሰድ
- ሲጃራ እና አደንዛዥ እፅ መውሰድ ሲሆን በሂደት ራስን ወደ ማጥፋት ያመራሉ

3. ግብረ ሰዶማዊነት እና ቀላጭነት
4. ከነዚ በተጨማሪ ጥቅም የሌላቸው ወደ ሀገራች በመግባት ሂደት ላይ ያሉ በዓላት አሉ ለምሳሌ፦ ቤቢ ሻወር፣ታንክስ ጊቪንግ፣ሃለዊን፣ፕሮም፣

1. <u>ዮጋ</u>

- የሳንስክሪት (የሳውዝ ኤዥያ ቋንቋ) ቃል ሲሆን ትርጉሙ ከኢነዱ መንፈስ ጋር የሚደረግ ውህደት ነው።

- የሂንዱ እምነት አስተምሮ ነው። አተገባበሩም ለሂንዱ አምላክ የመገዛት ፍቃደኝነት የሚገለጽበት ወይም መስዋዕት ነው።

- በሂንዱ እምነት በዚህች ምድር ከገነት ጋር የሚተካከል አንድ አለም አቀፍ ማህበር ወይም ህብረት አለ ተብሎ ይታመናል የዚህ አለም ቀፍ ህብረት አባል መሆን ያልቻለ ሰው እውነተኛ ደስታን አያገኝም ብለው ያስባሉ ዮጋም ይህንን በሂንዱ እምነት ከገነት ጋር የሚተካከል የአለም አቀፍ ህብረት ለመቀላቀል የሚረዳ መንገድ ነው።
- በተለያዩ የአለም ሀገራትና በእኛም ሀገር ዮጋ የስፓርት እንቅስቃሴ እንደሆነ ተደርጎ የሚነገርና በተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ስልጠና የሚሰጥ ቢሆንም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከአቀማመጡ ጀምሮ በዮጋ እንቅስቃሴ ትምህርት ውስጥ የሂንዱ እምነት አስተሳሰቦች ተካተው አብረው ይሰጣሉ።

መ የመጤባሕሎች መግቢያ መንገዶች

1. ለሕፃናት እና ታዳጊዎች

ሀ. የስልክ እና የቪዲዮ ጌሞች

- የጌሞቹ አሸናፊ ለመሆን ገጸ ባሕርያቱንበጭካኔ በገጀራ በጥይት እና በቦምብ መግደል ይጠይቃል ይህም ልጆቹ ጭካኔ : ወንጀለኝነእና ትጀብደኝነት እንዲለማመዱ ያደርጋል
- የጌሞቹ አሸናፊ ሲሆኑ እርቃን የሆነች ሴት ይቀርብላቸዋል አልያም ሙዚቃ ይጋበዛሉ

ለ. ፊልሞች

- ተወዳጅ የሕፃናት የካርቱን ፊልሞች ግብረ ሰዶማዊ ገፀ ባሕርያት ማካተት ከጀመሩ ቆይተዋል(ለምሳሌ ሲምፕሰን)
- በሀገራችን በአሁን ሰዓት በየመንደሩ በፍላሽ ዲስክ የሚቀርቡ ተከታታይ ፊልሞች ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ዝሙትን:የአደንዛዥ እፅን : ግብረ አውናንን:ግብረ ሰዶማዊነትን እና ሌሎች ከክርስትና መንገድ የሚያስወጡ ተግባራትን በስፋት ያካትታሉ

- በሀገራችን በስፍት የሚታዩ ግብረሰዶማዊ ትዕይንት እና ገፀ ባሕርያት የተንሰራፉባቸው ተከታታ ፊልሞች መካከል
- ማህበራዊ ሚዲያ(በቻት የሚደረግ ዝሙት፡ እርቃን ትዕይንት፡ ፍትወታዊምልልስ)በዩቲዩብ የእርርቃን ዳንስ የወንድ እና ሴት ግብረ ሰዶማውያን ትዕይንቶች

2. ለተማረው ክፍል

ሀ. በስልጠና እና ትምህርት

- በመማርያ መፅሃፍት እና በስልጠና ማኑዋሎች(ስነ ተዋልዶ እና የኤች አይቪ መከላከል በማስተማር ሰበብ ዝሙት፡ውርጃ፡ግብረ አውናን(ኮንዶም በማበረታታት
- በሲንፖዝየም እና ወርክሾፕ(መጤ ግኀጂ በሓላትን ለማስተዋወቅ እና ለማስረፅ በሚዘጋጁ የማስረፅ ውይይቶች እናከፍተኛ ፈንድ የሚደረግ

የሕፃናት ተጋላጭነት በመዋለ ሕፃናት(k.G)

1) የሕፃናት የፋሽን ሾው

- በትምህርት ቤት በሚከበሩ ቀናት ሕፃናት እርቃናቸውን ሆነው እየተውረገረጉ በአፈንጋጭ ዳንስ እና ዘፈን ታጅበው ይወጣሉ
- ተመልካቹ የሚሰጣቸው ደማቅ አድንቆት እና ጭብጨባ ለቁሳዊነት እና ስጋዊ ውበት ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርርጋቸዋል
- በ/ት ቤት በሚከበሩ በተለያዩ የበዓል ቀናት በቅጥ የለሽ ፅያፍ የውጭ ሙዚቃዎች በመታጀብ ከሕፃን ቀርቶ ከትልቅ ሴት ለማየት የሚከብድ ጭፈራ ያሳያሉ ለዝሂም አድናቆት እና ሽልማት ይቀርብላቸዋል
- በበርካታ ትምህርት ቤቶች የገናን በዓል ፍጹም አውሮፖዊ እና ስጋዊ አድርገው እንዲያከብሩ በማድረግ ፃምን:ቁጥብነትን: ስነምግባርን. . . ወዘተ እያስጣሉ ይገኛሉ
- አማርኛ እና ሌሎች የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች መናገር ቅጣት በሚያሰጥባቸው የግል ት/ት ቤቶች የማነት ቀውስ ውስጥ የተዘፈቁ እና ለራሳቸው ክብር የሌላቸው ዜጎች ይፈራሉ

ምንተ ንግበር

1. እየዳበረ የመጣውን ግለኝነት ማህበራዊ ትስስርን በማጥበቅ መከላከል።
2. ኢኮኖሚያዊ ትስስር በመፍጠር እርስ በእርስ የመረዳዳት ባሕልን ማጎልበት።
3. ሕፃናትን በኦርቶዶክሳዊ ሰብእና ኮትኩቶ ማሳደግ።
4. ትምህርት ቤቶች ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ በጎ ተፅህኖ ማሳደር።
5. ታዳጊዎችን ወደ ንሰሐ አባት ማቅረብ እና በግፅ ማማከር።
6. የታዳጊ እና ወጣቶችን የጠባይ ለውጥ መከታተል እናማወያየት።
7. ትንሿን ቤ/ክ በቤት ውስጥ መመስረት።